# ቦሼን ምን ነካው? ባሰበት እኮ!!!

ሰው ሲመራና ሲመራ (ለስልጣን ለማለት ፈልጌ ነው) መቼም ለየቅል ናቸው። ስልጣን ይዞ ህዝብን ማስተዳደር ሲጀምር 99 በመቶ ሊባል ይችላል የሰው ልጅ ባህሪው ይቀየራል በይበልጥ እንደእኛ ሃገር ታዳጊ በሆኑት ላይ። ግለሰቡ ስልጣኑን ሲጨብጠው ህዝብ መሆኑን ይረሳና ሁሌም ባለስልጣን እንደሆነ የሚቀር ይመስለዋል፤ ነገር ግን ወደ ህዝብነቱ የተመለሰ ቀን ወየውለት ነው የሚባለው ሌላ ምን ይባላል። ኧረ እስቲ ወደ ቦሼዬ ልምጣ!

አቶ ቦሼ በዚህ ወር ለፓርላማው በዲሲ ዲያስፖራዎች የተደረገውን የኢምባሲ ወረራ ሲናገሩ ሰምቼ በሳቅ የሞትኩ መሰላችሁ ነገረ ስራቸው እርር ድብን ነው ያደረገኝ (ለሳቸው ሞራል ስል ነው እርር አልኩ ያልኩት፤ካፈለጉ ርሳቸው ከነጦሳቸው እርር...)። ምን ቢሉ ጥሩ ነው በውጭ ሃገራት መኖር ሳይሳካላቸው ሲቀር የሻዕቢያ ቅጥረኛ ሆነው በመላላክ እያሸበሩ፣ እንዲሁም የሻዕቢያን ፍርፋሪ እየለቀሙ የሚኖሩ ቅጥረኞች፣ ገዳዮች እያሉ በዲሲ የደረሰባቸውን ሽንፈት ሲያስተባብሉ፣ ሌላም ሌላም...። ታዲያ ይሄኔ ነው አቶ ቦሼን ኧረ ትልቅ ሰው ነዎት ሼም፣ ሼም ያልኳቸው። ሙች ይሰማሉ!!! አንዴ ፈርዶባቸው የራዕዩ መሪ መንፈስ ተጠናውቷቸው። እኔን ምን እንደገረመኝ ታውቃላችሁ? የሻዕቢያን ፍርፋሪ እየለቀሙ ያሏት ነገር!!! ለመሆኑ ሻዕቢያ እንኳን ለኢትዮጵያኑ ፍርፋሪ ልትሰጥ ለራሷ የሚላስ የሚቀመስ የሌላት መሆኗን የአደባባይ ሚስጥር ነው። እናም የምትበላው የላት የምትከናነበው አማራት ሆነብኝ ሻዕቢያ ለአቶ ቦሼ። ገዳዩስ ማን ሆነና፣ አየነው እኮ ወዲን በደደቢት የለመደውን በአሜሪካ ሲደግመው። በአለም አቀፍ ደረጃ አሸባሪ ብሎ የተመደበው ህውሃት ወያኔ እንጂ ምስኪኑ ዲያስፖራ አይደለም። ጥሩ ሰው ነበሩ ይባላል ዱሮ ድሃ ሆነው፣ምን ነካዎት? ልቦናና የሚያስብ ጭንቅላት ቢኖርዎት ኖሮ እነኝህ ያልተሳካላቸው አሸባሪ የተባሉት ኢትዮጵያኖች የሚልኩት ብርና ሃገሪቷ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ባላጋንን ከዋናው ኤክስፖርት ምርታችን ቡና ባይበልጥ ነው!!! ይህን እንኳን ማገናዘብ ነበረብዎት።

ሌላው ቅጥፈታቸው የኢትዮጵያ መንግስትና ሌላው ኢትዮጵያዊ (የወያኔ ደጋፊ ማለታቸው ነው) ከገዳዮቹ ማለትም ከአሸባሪዎቹ ጋር ግብግብ የፈጠሩበት አንድም ጊዜ የለም ... አቦ ትንሽ ይደብርዎታ! ውሸትም ሲበዛ እኮ!!!! ከቪዲዮ በላይ መረጃ ምን አለ? አቶ ቦሼ ከበታች የለጠፍኳቸውን ቪዲዮዎች ጋበዝኩዎት ሌላ ምን ይባላል፣ ያዘንኩት ግን ያች የተቀደሰች ሃገር በርስዎ ቀጣፊ ስትመራ በጣም ያሳዝናልም ያሳፍራልም!!! የምመክርዎ በዱሮ አለቃዎት ላይ ምን እንደደረሰ ያስቡና ወደ አዕምሮዎት ይመለሱ። ካስታወሱ ባለራዕዩ መሪዎት እጅ እንቆርጣለን፣ ባንዲራ ጨርቅ ነው፣ ሌላም ሌላም ያሉበት ልሳን ተዘግቶ ምንም ሳይሉን ላሽ ብለዋል።

ኧረ ደግሞ ክቡር የሆነው ባንዲራችንን መሬት አውርደው ሲሉ ትንሽ ትንሽ አይሰቀጥጥዎትም? ደፋር ነዎት፣ ምን ያድርጉ የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛዋል አይደል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆነ የወደቀ ዛፍ ሆኗል ማንም እንደልቡ እየመጣ ይፈነጭብናል። ፊቱን ያዞረ ቀን ግን ...። ባልደረባዎ ባንዲራ ጨርቅ ነው እያሉ እንዳላፌዙብን እርስዎ ደግሞ ዞር ብለው ክቡሩ ባንዲራ ይሉናል... ፌዝ አይሆንም? ህዝብስ ላይ ማላገጥ አይሆንም? ለማንኛውም ጊዜ ይፈታዋል።

አቶ ቦሼ (ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ ቦሼ) በአርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ዲን ሆነው ሲሰሩ በጣም መልካምና ትሁት እንደነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ሲናገሩ ሰምቻለሁ። ታዲያ አሁን ምን ነክቷቸው ነው ውሸት፣ ቅጥፈት ያበዙት። ከአህያ የዋለች ጊደር ሆኖባቸው ይሆን? እንደዛ ከሆነ አሁንም ጊዜ አለዎትና እራስዎትን ከወያኔ ቅጥፈትና ንቀት ትምህርት ቤት አውጥተው ወደ ህዝቡ ይመለሱ። አለበለዚያ ግን ስልጣንዎትን ተመክተው እንደፈለጉ የሚያፋሽጉ ከሆነ ህዝብ የሆኑ እለት ምን እንደሚገጥምዎ ግልፅ ነው። እናም አቶ ቦሼ ወደ ህሊናዎ ይመለሱ!!!

አሜጋ ነኝ ከኖርዌይ (chinchaw94@gmail.com)